የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፯
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.37
ADDIS ABABA 22nd April, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፺፩/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

ለሁለተኛው የኢትዮጵያ የዕድገት እና የተወዳዳሪነት የልማት ፖሊሲ ፋይናንስ ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……ገጽ ፲፪ሺ፭፻፲፮

## Content

Proclamation No.1191/2020

International Development Association Financing Agreement for Financing the Second Ethiopia Growth and Competitiveness Programmatic Development Policy Ratification Proclamation …………………………….....................Page 12,516

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፺፩/፪ሺ፲፪

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሁለተኛው የኢትዮጵያ የዕድገት እና የተወዳዳሪነት የልማት ፖሊሲ ፋይናንስ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ፩፻፴፮ ሚሊዮን ፬፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ ሰላሳ ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፪ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው ልዩ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1191/2020

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Financing Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association shall provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan an amount equivalent to 136,400,000.00 Special Drawing Rights (One Hundred Thirty Six Million Four Hundred Thousand SDR) for financing the Second Ethiopia Growth and Competitiveness Programmatic Development Policy, was signed in Addis Ababa on 23rd day of March 2020;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its special session held on the 10th day of April, 2020

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ “ለሁለተኛው የኢትዮጵያ የዕድገት እና የተወዳዳሪነት የልማት ፖሊሲ ፋይናንስ ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም አቀፍ የልማት ማህበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፺፩/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማህበር መካከል መጋቢት ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 6564-ET በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፩፻፴፮ ሚሊዮን ፬፻ ሺህ ኤስ.ዲ.አር (አንድ መቶ ሰላሳ ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ.አር.) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the “International Development Association Financing Agreement for Financing the Second Ethiopia Growth and Competitiveness Programmatic Development Policy Ratification Proclamation No. 1191/2020”.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Financing Agreement Number 6564-ET signed in Addis Ababa on 23rd day of March 2020 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan an amount equivalent to 136,400,000.00 Special Drawing Rights (One Hundred Thirty Six Million Four Hundred Thousand SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force up on its publication in the *Federal Negarit Gazettee.*

**Done at Addis Ababa, on this 22nd day of April, 2020**

**SAHLEWORK ZEWD**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**